# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ

## የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርስቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች

ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

**ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣**

የዩኒቨርስቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**የገቢ ሂሳብ፣**

1. ዩኒቨርስቲው በግቢው ውስጥ የሚገኙትን የመመገቢያ ቤቶችን እና የኮንቴነር ሱቆች ለተለያዩ አገልግሎቶች በውል ያከራየ ቢሆንም፣ በድምሩ ብር 22,215.47 ያልሰበሰበ መሆኑን፣

2. ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ጋር በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ ለተለያዩ አገልግሎት የሚሆኑ የኮንቴነር ሱቆችን በውል ያከራየውን የገቢ ሂሳብ ለዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ህብረት እንዲሰበስብ በመደረጉ መንግስት ማግኘት ያለበትን ገቢ ብር 32,100.00 እንዳያገኝ ያደረገ አሰራር መሆኑንና ገቢው በህጋዊ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ እንዲሰበሰብ ያልተደረገ መሆኑ፣

**<u>የወጪ ሂሳብ፣</u>**

3. የዩኒቨርስቲው ሰራተኞች ከተመደበላቸዉ የአልጋ አበል በተጨማሪ በቀን ብር 100.00 ሂሳብ በድምሩ ብር 14,400.00 ከውሎ አበሉ መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
4. ዩኒቨርስቲው በውሉ ሳይካተት (ሳይኖር) በድምሩ ብር 53,164.00 የትራንስፖርት ክፍያ ለመምህራኑ አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
5. ዩኒቨርስቲው በድምሩ ብር 3,815,199.61 አለአግባብ ከመንግስት መመሪያ ውጭ ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅም እና የልዩ አበል በሚል ክፍያ የከፈለ መሆኑን፣
6. ዩኒቨርስቲው ለተለያዩ መኪናዎች መለዋወጫ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎችን ለመግዛት ባወጣው ግልፅ ጨረታ አሸናፊ ድርጅት ዕቃዎችን በውሉ መሰረት በተባለው ቀን ባለማስገባቱ ያስያዘው የውል ማስከበሪያ ዋስትና በቅጣት መልክ ተወርሶ ወደ ዩኒቨርስቲው ሂሳብ ገቢ ተደርጎ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በ2008 በጀት ዓመት ፈሰስ ማድረጉን እየታወቀ ከአንድ ዓመት በኋላ ምንም ዓይነት ምክንያትና የሰነድ ማስረጃ ሳይኖር፣ የተወረሰው ብር 47,564.00 አለአግባብ ለድርጅቱ ተመላሽ የተደረገ መሆኑን፣
7. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 8,527,300.59 የመሬት የይዞታ ኪራይ፣ የዕቃ ግዥ፣ ለባለሙያዎች የተረኝነት አበል ክፍያ እና የአገልግሎት ክፍያን አገልግሎቱ በተገኘበት በጀት ዓመት መክፈል ሲገባው በ2009 በጀት ዓመት ክፍያ የፈፀመ መሆኑን፣

8. ዩኒቨርስቲው ውሉን ከተዋዋለበት ቀን ጀምሮ ምንም አይነት የዋጋ ለውጥ የማይኖር መሆኑን በውሉ በግልፅ ተቀምጦ እያለ ከውሉ ውጭ በድምሩ ብር **1,192,455.00** ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
9. ዩኒቨርሲቲው በብር 1,396,148.00 ብዛቱ 4 ኮንቴይነር የህክምና ዕቃዎች ከሁማን ብሪጅ በእርዳታ ለመጣ የትራንስፖርት ወጪውን ለድርጅቱ ሲከፍል ንብረቱ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት ተገኝቷል፡፡
10. ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ወጪዎችን በትክክለኛው የሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው በድምሩ ብር 1,446,897.63 ያለ ሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፣
11. ዩኒቨርስቲው የኮምፒዩተርና የመጽሃፍ ግዥ ብር 681,024.00 የወጪ ደረሰኝ ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣
12. ዩኒቨርስቲው ለጤና ሳይንስ ኮሌጅ ባለሙያዎች እና ለደብረ ታቦር ሆስፒታል ሀኪሞች የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪዎችን የትርፍ ሰዓት ያስተማሩበት በሚል ከተፈቀደው ውጭ በድምሩ ብር **965,840.59** ውል ሳይኖር መንግስት ከፈቀደው የክፍያ መጠን መመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑን፣
13. ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ዕቃዎች ከተለያዩ ድርጅቶች በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም ሲገባው በድምሩ ብር 6,843,833.50 ከግዥ መመሪያ ውጭ ያለውድድር በቀጥታ ግዥ የፈፀመ መሆኑንና አሸናፊ ተብሎ የተሰጠው ድርጅት የአስመጭነት ፍቃድ የሌለው መሆኑ እየታወቀ ጨረታውን እንዲያሸንፍ የተደረገ መሆኑን፣
14. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 518,340.00 ከአንደኛ አሸናፊ ባለመግዛቱ አላግባብ ተጨማሪ ወጪ የመንግስት ገንዘብ እንዲወጣ ያደረገ መሆኑን፣
15. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ የብር 2,764,197.09 ግዥ የፈፀመው በዘርፉ በቂ አቅራቢ እያለ በግልፅ ጨረታ መግዛት ሲገባ ከግዥ መመሪያ ውጭ በውስን ጨረታ ግዥ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑን፣
16. ዩኒቨርስቲው ከአንድ አቅራቢ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ካልሆነ ድርጅት በድምሩ በብር 222,874.00 ከግዥ መመሪያው ወጭ የአገልግሎት ግዥ ተፈፅሞ የተገኘ መሆኑን፣

17.ዩኒቨርስቲው በድምሩ የብር **11,343,518.68** ግዥ በቀጥታ አገልግሎቱን ከሚሰጠው ድርጅት ውል በመዋዋል ያለውድድር ወይም ከሚመለከተው አካል በልዩ ሁኔታ ሳያስፈቅድ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

18.ዩኒቨርሲቲው ለፕሬዝዳንት ፅ/ቤት የቦርድ አመራር የነበሩትን እና ም/ፕሬዝዳንቶችን ለመሸኘት የሚውል ባለ 21 ካራት እያንዳንዱ 10 ግራም የሆነና ብዛቱ 10 የውጭ በሚል ብር 124,775.00 ከመመሪያ ውጭ ያለአግባብ ግዥ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑን፣

19.ዩኒቨርሲቲው ፕሮጀክቱን ከመረከቡ በፊት የነበሩ አግባብነት ያላቸው ሰነዶችና መረጃዎች ጉዳዩ ከሚመለከተው ከትምህርት ሚ/ር ርክክብ ባለመደረጉና በዩኒቨርሲቲው በመያዣነት የተመዘገበ ሂሳብ ሳይኖር ለአምደሚካኤል ተመስገን ጠ/ሥ/ተቋራጭ ምእራፍ 1 ሎት ኤ መሰረተ ልማት ግንባታውን አጠናቆ የመጨረሻ ዙር ርክክብ ስላደረገ በማለት የመያዣ ሂሳብ ብር 1,240,730.13 የተከፈለው መሆኑን፣

20.ድርጅቱ የፕሮጀክቱ ግንባታ በማዘግየቱ ምክንያት ብር 14,280,576.95 የጉዳት ካሣ /Liquidation Dameg/ ገቢ ሳያደርግ ወይም ሳይቀነስበት የተገኘ መሆኑን፣

21.ዩኒቨርሲቲው ለአባይ ደምሴ ህ/ሥራ ተቋራጭ Lab & Class Room ግንባታን በብር 30,168,566.27 ውል ያሰረ ሲሆን ተለዋጭ ሥራ /Variation Order/ የ30% ብር 9,050,569.88 መሆን ሲገባው፣ ብር 12,814,146.40 ከ30% በላይ በመሆኑ 12,814,146.40 - 9,050,569.88 = ብር 3,763,576.53 ለተለዋጭ ሥራ መመሪያው ከሚፈቅደው በላይ ያለአግባብ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑን፣

22.በዩኒቨርሲቲው የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ስራ አስኪያጅ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል/በኮንስትራክሽን ሚ/ር/ የተረጋገጠ አማካሪ መሃንዲስ ለመሆን የሚያስችል ሰርተፊኬትና ፍቃድ ሳይኖራቸው የብር **70,679,377.44** ግንባታዎች የክፍያ ሰነዶችና የክፍያ የምስክር ወረቀት /Payment Certificate/ እያጸደቀ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣

<u>**የተሰብሳቢ ሂሳብ፣**</u>

23. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 35,129,439.63 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ እና በመመሪያው መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

**የተከፋይ ሂሳብ፣**

24. በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ ከሚታይ ብር 5,356,012.34 ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ በተከፋይ የተያዘ እና ለትምህርት/ሚ/ር መከፈል የሚገባው ብር 4,450,208.45 ለባለመብቱ ሳይከፈል ወይም ሳይወራረድ ከ4 ዓመት በላይ መቆየቱን፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 24 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት ዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣**

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው ከጨረታ ሰነድ ሽያጭና ከቅጣት የተሰበሰበ ገንዘብ በድምሩ ብር 1,262,179.87 ለገንዘብና ትብብር ሚ/ር ገቢ መደረግ ሲገባው፣ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ገቢ መደረጉ፣

- ዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተመደበው የወጪ በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር በየፕሮግራሞቹ ከ10% በላይ ከመደበኛ በጀት ብር 19,765,255.77 እንዲሁም ከካፒታል ብር 71,555,739.47 በድምሩ ብር **91,320,995.24** ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑን፣

**ሌሎች ጉዳዮች፣**

- የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት ክፍል በመዋቅሩ በተፈቀደው መጠን በሰው ሀይል ያልተደራጀ መሆኑን፣
- በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው የንብረት አስተዳደር ሲታይ በንብረት ደንብና መመሪያ መሠረት ዕቃዎች በአግባቡ ያልተያዙና ያልተወገዱ እንዲሁም የተዘረጋ የንብረት

ቁጥጥር ስዓርት ባለመኖሩ ለረዥም ጊዜ በመቀመጣቸው ለብክነት እየተዳረገ መሆኑን፣

- ዩኒቨርሲቲው ካሉት 33 ተሽከርካሪ መኪናዎች ውስጥ በኪ/ሜትር የሚጠቀሙት ነዳጅ ከልኬቱ ጋር ሲመዛዘን 29 ተሽከርካሪ በመብለጥ እና 4 ተሽከርካሪ በማነስ የሚያሳይ በመሆኑ ልኬቱን በትክክል እንደማይሰራ የተገኘ መሆኑን፣
- የሰሌዳ ቁጥር ኢት-④-18517 ኢቬኮ ቱርቦ የጭነት መኪና ሊብሬ የሌለው መሆኑን፣
- ሞተር ሳይክል ያማሃ ኢት-④-0524 ያለአገልግሎት ከሁለት ዓመት በላይ የተሽከርካሪ መለዋወጫ ንብረት ክፍል ውስጥ ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፣
- በዩኒቨርሲቲው በጀት የተሰሩ ህንጻዎች በዋናው ግቢ፣ በደብረ ታቦር ሆስፒታል፣ በአዲስ ዘመን ሆስፒታል፣ በእስቴ ሆስፒታል፣ በግንቦት 20 ጤና ጣቢያ፣ በደብረ ታቦር ጤና ጣቢያ፣ በህዳር 11 ጤና ጣቢያ እና በአውዘት ምርምርና አገልግሎት ህንጻዎች ግንባታቸው ተጠናቆ ርክክብ ሲደረግ፣ በመመሪያው መሰረት እንደቋሚ ንብረቶች በተለየ መዝገብ ያልተመዘገቡ መሆኑን፣
- የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ላይ እርምጃ አወሳሰድ፣
  - ብር 2,500,000.00 ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመለት ዓላማ ውጭ ለሆነ የሥራ ዘርፍ ከመደበኛ ባልተፈቀደ በጀት ወጪ በማድረግ አለአግባብ የአክስዮን ግዥ መፈጸመ መሆኑና ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ፣
  - በ27/01/2007 በቁጥር በጠ1/6/39 ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተላለፈ መመሪያ መሰረት በመንግስት ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ ተማሪዎች ካለው ነባራዊ ሁኔታ አኳያ በመገምገም ከመስከረም 1ቀን 2007 ጀምሮ የምግብ በጀት ተመን በተማሪ በቀን ብር 15 እንዲሆን የተወሰነ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው ለ2ኛ እና ለ3ኛ ዓመት ህክምና አንስቴዥያን ሚድዋይፈሪ ተማሪዎች በቀን ብር 35 እንዲሰጣቸው በመደረጉ እና ለእያንዳንዱ ተማሪ ብር 20 በተጨማሪ በመከፈሉ በድምሩ ብር 242,800.00

ከተመን በላይ ወጪ መደረጉና አለአግባብ በብልጫ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ፣

- የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ/በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ቢወስንም ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 137,999.96 የማበረታቻ እና ሽልማት ክፍያ ፈፅሞ መገኘቱና አለአግባብ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ፤

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ

# የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

**መግቢያ፣**

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

**ዓላማ፣**

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

**የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣**

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣

- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ፤ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የተቋሙ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>የገቢ ሂሳብ፣</u>

1.1 <u>ግኝት፣</u>

የፌደራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል አራት የመንግስት ገቢ አሰባሰብና ወደ ተጠቃለለ ፈንድ ገቢ ለማድረግ አንቀጽ 3 በመንግስት ስም የተሰበሰበውን ገንዘብ ወደ ተጠቃለለ ፈንድ ገቢ ስለማድረግ ንዑስ አንቀጽ 1-2 ማንኛውም በመንግስት ስም የተሰበሰበ ገንዘብ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ወይም በመስሪያ ቤቱ ስም ወደተከፈተው የገቢ መሰባሰቢያ ባንክ ሂሣብ ገቢ መደረግ አለበት ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው:-

- በሂሣብ መደብ 1489 በተለያየ ጊዜ ከጨረታ ሰነድ ሽያጭና ከቅጣት የተሰበሰበ ገንዘብ በድምሩ ብር 1,262,179.87 ለገንዘብና ትብብር ሚ/ር ገቢ መደረግ ሲገባው፣ ለገቢዎችና ጉሙሩክ ባለሥልጣን ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ገቢ መደረጉ፣
- ዩኒቨርስቲው በግቢው ውስጥ የሚገኙትን የመመገቢያ ቤቶችን እና የኮንቴነር ሱቆች ለተለያዩ አገልግሎቶች በውል ያከራየ ቢሆንም ብር 22,215.47 ያልሰበሰበ መሆኑን፣
- የፌደራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል አራት የመንግስት ገቢ አሰባሰብና ወደ ተጠቃለለ ፈንድ ገቢ ስለማድረግ ቁጥር 2/1 የመንግስት ገንዘብ ለመቀበል ወይም ለመሰብሰብ የሚችለው በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ገንዘብ ለመሰብሰብ ውክልና በተሰጠው ቋሚ የመንግስት ሰራተኛ ብቻ መሆን እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ ነገር ግን ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ጋር በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ ለተለያዩ አገልግሎት የሚሆኑ የኮንቴነር ሱቆችን በውል ያከራየውን የገቢ ሂሳብ ለዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ህብረት

እንዲሰበስብ በመስጠቱ በተወሰደው ናሙና መንግስት ማግኘት ያለበትን ገቢ ብር 32,100.00 እንዳያገኝ ያደረገ አሰራር መሆኑንና ገቢው በህጋዊ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ እንዲሰበሰብ ያልተደረገ መሆኑ፣

ተረጋግጧል፡፡

### 1.2 ስጋት፣

መንግሥት ማግኘት የሚገባውን ገንዘብ እንዳያገኝ ከማድረጉም በላይ በስራ ላይ የዋለውን የመንግስት መመሪያ ሊጥስ ይችላል፡፡

### 1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ከውስጥ ገቢ አርዕስቶች የተሰበሰበው ገንዘብ ለዚሁ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ በተገቢው ገቢ እንዲሆን ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡
- በዩኒቨርሲተው ገንዘብ የመሰብሰብ ሥልጣን በተሰጠው ሠራተኛ እንዲሰበሰብ ማድረግ ይገባዋል፡፡
- ሳይሰበሰብ የቀረው የኪራይ ገቢ ተሰብስቦ ለዩኒቨርስቲው ገቢ ሊደረግና ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

### 1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

- አስተያየቱ ከተሰጠ በኋላ ይህ አሰራር እንዲቆም ተደርጓል፣
- በአስተያየቱ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ተወስዷል፣
- በተማሪዎች ህብረት ሲሰበሰብ የነበረውን አሰራር በማስቆም በዩኒቨርሲቲው በፋይናንስ በኩል እንዲሰበሰብ ተደርጓል፣

## 2 የወጪ ሂሳብ፣

### 2.1.1 ግኝት፣ ከመመሪያ ውጭ ለመኝታ አበል ተከፍሎ የተገኘ፣

በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 መሰረት ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ሠራተኞች የደመወዝ መደብና ጥቅማ ጥቅም ቀርቦ የሚወሰነው በሚኒስትሮች ምክር ቤት መሆኑ የተደነገገ መሆኑንና ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር/ሲሰሚ/30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/2003 ከደንብና መመሪያ ውጭ እየተከፈሉ ያሉ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በአስቸኳይ እንዲቋረጡ መመሪያ የተላለፈ መሆኑ

ይታወቃል:: ይሁን እንጂ የዩኒቨርስቲው ሰራተኞች በተለያየ ጊዜ ከቦታ ቦታ በሚንቀሳቀሱበት እና በሚያድሩበት ጊዜ ከተመደበላቸዉ የአልጋ አበል በተጨማሪ በቀን ብር 100.00 ሂሳብ በድምሩ ብር 14,400.00 ከመመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

2.1.2 ስጋት፣

- መንግስት በተለያየ ጊዜ የሚያወጣቸው አዋጆችና መመሪያዎች ተግባራዊ ላይደረጉ ይችላሉ፡፡
- የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- ከህግ እና መመሪያ ውጭ የሆኑ ውሳኔዎችን በመስጠት የሚከፈል ሂሳብ ተጠያቂነት ሊያመጣ ይችላል፡፡

2.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ያለአግባብ ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለዉ የአልጋ አበል ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም የመንግስት የክፍያ መመሪያዎች ተጠብቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

2.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ለሹፌር ይከፈል የነበረው የአልጋ አበል እንዲቆም ተደርጓል፣

2.2.1 ግኝት፣ ለተጋባዥ መምህራን ከውል ውጭ ተከፍሎ የተገኘ፣

ዩኒቨርስቲው የተለያዩ ውሎችን ሲያደርግ እና ክፍያ ሲፈፅም በውሉ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ከተጋባዥ መምህራን ጋር በተደረገ ውል ከ16/02/09 እስከ 23/02/09 ፈተና ለማውጣት፣ ለመፈተን፣ ውጤት ለመሙላት እና የትምህርት ሂደት ለመገምገም የሚደረግ ክፍያ ብር 13,500.00 እንደሆነ በውሉ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን በውሉ ሳይካተት (ሳይኖር) በድምሩ ብር **53,164.00** የትራንስፖረት ክፍያ ለመምህራኑ አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

2.2.2 ስጋት፣

- በመመሪያ መሰረት ክፍያ ካልተፈፀመ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- የውሉን ታማኝነት እና ተፈፃሚነት ሊያሳጣ ይችላል፡፡

2.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ ክፍያ ሊፈፀም ስለሚገባ ከውሉ ውጭ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች ተመላሽ ሊደረጉ እና ለወደፊትም ጥንቃቄ ሊወሰድ ይገባል፡፡

2.2.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ለወደፊቱ በውል እንዲካተት ተደርጓል፣

2.3.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም፣</u>

በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 መሰረት ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ሠራተኞች የደመወዝ መጠንና ጥቅማ ጥቅም ቀርቦ የሚወሰነው በሚኒስትሮች ምክር ቤት መሆኑ የተደነገገ መሆኑን እና ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር/ሲሰሚ/30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/2003 ከደንብና መመሪያ ወጭ እየተከፈሉ ያሉ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በአስቸኳይ እንዲቋረጡ መመሪያ ተላልፏል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፣

- የከባድ መኪና ሹፌሮች እና ረዳቶች በየወሩ የቶፕ አፕ እና የልዩ አበል ክፍያ በድምሩ ብር **233,900.00** ከደንብና መመሪያ ውጭ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣
- በ24/10/2008 ዓ.ም በተያዘ ቃለ-ጉባኤ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህራን የሀምሌ እና የነሀሴ ወር የሚሰሩበት ኢለቨናይዜሽን በሚል ደመወዛቸው በእጥፍ እንዲከፈላቸው በመወሰን ለ97 መምህራን የሀምሌና የነሀሴ ወር የሰሩበት ኢለቨናይዜሽን በድምሩ ብር 1,686,432.00 የተከፈለ መሆኑን፣
- የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ባለሙያዎች በደብረ ታቦር ሆስፒታል የሰሩበት የተረኝነት አበል በሚል በድምሩ ብር 1,894,867.61 የተከፈለ ሲሆን፣

በጠቅላላው ብር 3,815,199.61 አለአግባብ ከመንግስት መመሪያ ውጭ የተከፈለ ለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

2.3.2 <u>ስጋት፣</u>

- መንግስት በተለያየ ጊዜ የሚያወጣቸው አዋጆችና መመሪያዎች ተግባራዊ ሳይደረጉ ይችላሉ፡፡
- የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- ከህግ እና መመሪያ ውጭ በመወሰን የሚከፈል ክፍያ ተጠያቂነት ሊያመጣ ይችላል፡፡

### 2.3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ቦርድም ሆነ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተለያዩ ውሳኔዎችን ሲሰጡ መንግስት የሚያወጣቸው አዋጆችና መመሪያዎች ተግባራዊ ማድረግን ይኖርባቸዋል፡፡ ያለአግባብ ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለው ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም የመንግስት የክፍያ መመሪያዎች ተጠብቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

### 2.3.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- አሰራሩ እንዲቆም ተደርጓል፣
- የህክምና ትምህርት በተፈጠሮው ከ11 ወር በላይ የሚፈጅ ሲሆን በተለይ የ1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ፣ 4ኛ ፣ 5ኛ ዓመት ተማሪዎች በካሪኩለሙ የተነሳ ወጥ በሆነ ሰዓት እረፍት ስለማይኖራቸው መምህራኑ ዓመቱን በሙሉ ሥራ ላይ ናቸው ይህ ደግሞ የሐምሌ እና የነሐሴ ወር እረፍት እንዳይኖራቸው በመደረጉ በእረፍት ከሚያገኙት ደመወዝ በተጨማሪ የወር ደሞዛቸው እንዲከፈላቸው ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የጤና ሳይንስ ኮሌጆች ወጥ አሰራር ሆኖ እየተተገበረ ነው፣
- ተማሪዎቻችን በአሁኑ ሰዓት 5ኛ ዓመት ህክምና ት/ት የደረሱ ሲሆን እነዚህ ተማሪዎች Senior ሐኪሞች በ4ቱም የትምህርት ዘርፎች (ማህጸን፣ ቀዶ ጥገና፣ ህጻናት እና ውስጥ ደዌ) ተመድበው ተማሪዎችን ማታ በማደር በበሽተኞች ላይ የሚደረገውን የተግባር ትምህርት ማግኘት እንዳይችሉ ስለሚያደርጋቸው እና ከፍተኛ የሙያ ክፍተት ስለሚሆን ይህንን ችግር ለመፍታት የተወሰደ ነው፣

ዩኒቨርሲቲው የራሱ ሆስፒታል ቢኖረው ኖሮ ግን በተረኛው ሃኪም ሥለሚሸፈን ይህ ወጭ አይኖረውም ነበር፣

2.3.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

- የህክምና ትምህርት በተፈጠሮው ከ11 ወር በላይ የሚፈጅ ሲሆን እናም በእረፍት ከሚያገኙት ደመወዝ በተጨማሪ የወር ደሞዛቸው እንዲከፈላቸው ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የጤና ሳይንስ ኮሌጆች ወጥ አሰራር ሆኖ እየተተገበረ ነው፣ ለተባለው ያለው ችግር ሳይገባን ቀርቶ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የጤና ሳይንስ ኮሌጆች ወጥ አሰራር ሆኖ እየተተገበረ ስለሆንም አይደለም፡፡ ስለሆነም በመመሪያው መሰረት ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ስለተደረገ በራሳቹ ውሳንዬ ችግሩ ስለአለ ብቻ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ልትከፍሉ አትችሉም፡፡ በመሆኑም ለሚመለከተው አካል አስፈቅዳቹ መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡
- ከፍተኛ የሙያ ክፍተት ስለሚሆን ይህንን ችግር ለመፍታት የተወሰደ ነው፣ ዩኒቨርሲቲው የራሱ ሆስፒታል ቢኖረው ኖሮ ግን በተረኛው ሃኪም ሥለሚሸፈን ይህ ወጭ አይኖረውም ነበር፣ ለተባለው አሁንም ቢሆን ዩኒቨርሲቲው ለሚመለከተው አካል አስፈቅዶ መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡

2.4.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>አለአግባብ ተመላሽ የተደረገ የቅጣት ሂሳብ፣</u>

የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ሰኔ 2002 ክፍል 4 ንዑስ አንቀፅ 16. 25.3 የመንግስት መስሪያ ቤቱ አቅራቢው በውሉ መሰረት አለመፈፀሙን ሲያረጋግጥ በንዑስ አንቀፅ 16. 25.2 መሰረት አቅራቢው ያሲያዘውን የውል ማስከበሪያ ሙሉ በሙሉ መውረስ ይኖርበታል ይላል፡፡ በዚሁ መሰረት ዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ መኪናዎች መለዋወጫ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎችን ለመግዛት ባወጣው ግልፅ ጨረታ ላይ አባሆዬ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህበር የተባለው ድርጅት ማሸነፉ እና ውል ሲገቡ የብር 47,564.00 ዋስትና ያሲያዙ ሲሆን ከላይ የተጠቀሰው አሸናፊ ድርጅት ዕቃዎችን በውሉ መሰረት በተባለው ቀን ባለማስገባቱ ያሲያዘዉን የውል ማስከበሪያ በቅጣት መልክ ተወርሶ በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 494742 በቀን 10/06/08 ወደ ዩኒቨርስቲው ሂሳብ ገቢ

ተደርጎ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በ2008 በጀት ዓመት ፈሰስ መደረጉ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ከአንድ ዓመት በኂላ ምንም ዓይነት ምክንያትና የሰነድ ማስረጃ ሳይኖር በቀን 07/06/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 601579 የተወረሰው ይኸው ገንዘብ ብር **47,564.00** ለድርጅቱ ተመላሽ መደረጉን ለማወቅ ተችሏል።

2.4.2 **ስጋት፣**

- የውሉን ታማኝነት እና ተፈፃሚነት ሊያሳጣ ይችላል።
- ዕቃዎች በወሉ መሰረት ባለመግባታቸው መንግስት ሊያገኝ የሚችለዉን የጉዳት ካሳ ሊያሳጣ ይችላል።

2.4.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ውሉ ተፈፃሚ ሊሆን እና መንግሰትም ሊያገኝ የሚገባዉን ጥቅም ማግኘት ስለሚኖርበት አላግባብ ለድርጅቱ የተመለሰው ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ገቢ መደረግ ይኖርበታል።

2.4.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፣**

አባ ሆዴ የተባለው ድርጅት እቃ አቅርቦት በጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ ውድቅ የተደረገ ሲሆን በዚህ ጊዜ ያልያዙት ማስያዣ የተወረሰ ሲሆን ከዚያ በኋላ አስተካክለው በማቅረባቸው በጀት ዓመቱ ካለፈ በኋላ ወጭ አድርገን ከፍለናል ወደፊት ይህንን አሰራር እናስተካክላለን፣

2.5.1 **ግኝት፣ ያለበጀት ዓመቱ የተከፈለ፣**

የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 መሠረት የበጀት ዓመት ከሐምሌ1----ሰኔ 30 መሆኑን ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡-

- ብር 6,804,000.00 ለደ/ታቦር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ፅ/ቤት ከ2006 እስከ 2008 በጀት ዓመት የይዞታ ኪራይ፣
- ብር 933,706.00 ለሶላር የመድሀኒትና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ጅምላ ንግድ ለጤና ሳይንስ ትምህርት ክፍል አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎችን በ2008 በጀት ዓመት ገቢ ላደረጉት፣

- ብር 53,300.00 ከፋርጣ ወረዳ እና ከደ/ታቦር ከተማ አስተዳደር ለተዉጣጣ ካሳ ገማች ኮሚቴ ባስተባባሪነት እና በባለሙያነት ከመጋቢት 25/2008 ዓ.ም እስከ ግንቦት 4/2008 ዓ.ም ለሰሩበት አበል፣
- ብር 174,587.07 ለጤና ሳይንስ ኮሌጅ ባለሙያዎች በደብረታቦር ሆስፒታል በሰኔ ወር 2008 ዓ.ም የሰሩበት የተረኝነት አበል ክፍያ፣
- ብር 353,517.08 ለምንትዋብ አጥናፉ (ጋፋት ሆቴል) ዩኒቨርሲቲው በ2008 በጀት ዓመት ለተጠቀሙበት የመስተንግዶ ክፍያ፣
- ብር 208,190.44 ከመድሀኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የኬሚካል ግዥ በ2008 በጀት ዓመት ገቢ የተደረገ፣

በድምሩ ብር **8,527,300.59** የዕቃ ግዥን እና የአገልግሎት ክፍያን በበጀት አመቱ መክፈል ሲገባው ለዩኒቨርሲቲው ከተበጀተለት የ2009 በጀት ዓመት ላይ ክፍያ የፈፀመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

2.5.2 <u>ስጋት፣</u>

- የመንግስትን በጀት ከደንብና መመሪያ ወጪ መጠቀም የመንግስት መመሪያን ከመጣሱም በላይ የሒሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የበጀት ዓመቱን ወጪዎች እንዳያመለክት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- እንዲሁም በ2009 በጀት ዓመት ሊሰሩ የታቀዱ ስራዎችን ሊያስተጓጉል ይችላል፡፡

2.5.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ከመንግስት መመሪያና ደንብ ውጭ የሚከፈሉ ማናቸውም ክፍያዎች ተቀባይነት የሌላቸው በመሆኑ የበጀት ዓመቱን ግዢ በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ እና በወጪ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተት አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.5.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ለወደፊቱ ለማስተካከል እንሞክራለን፡፡ ነገር ግን /Foreign exchange/ ከውጭ ምንዛሬ ጋር ተያይዞ ዕቃው ስለሚዘገይ በዚህ ምክንያት ነው ችግሩ ወደፊትም ሊገጠም ይችላል፣

### 2.6.1 ግኝት፣ ከውሉ ውጭ ተከፍሎ የተገኘ፣

ዩኒቨርስቲው የተለያዩ ውሎችን ሲዋዋል እና ክፍያ ሲፈፅም በውሉ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ስናደርግ የውል ይዘቱ የፅዳት ስራ፣ የምግብ ዝግጅት እና የመስተንግዶ አገልግሎት ለማግኘት ከተለያዩ ማህበራት ጋር ውል ተዋውሎ በማሰራት ላይ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ውሉን ከተዋዋለበት ቀን ጀምሮ ምንም አይነት የዋጋ ለውጥ የማይኖር መሆኑን በውሉ ላይ በግልፅ ተቀምጦ እያለ ለነዚሁ ማህበራት ከውሉ ውጭ በድምሩ ብር 1,192,455.00 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

### 2.6.2 ስጋት፣

- በመመሪያ መሰረት ክፍያ ካልተፈፀመ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- የውሉን ታማኝነት እና ተፈፃሚነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡

### 2.6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ ክፍያ ሊፈፀም ስለሚገባ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች ተመላሽ ሊደረጉ እና ለወደፊትም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

### 2.6.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በውሉ ላይ አገራዊ የደመወዝ ለውጥ ሲኖር እንደምናሻሽል በተቀመጠው ውል መሰረት የተፈጸመ ነው፡፡

### 2.6.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በውሉ ላይ አገራዊ የደመወዝ ለውጥ ሲኖር እንደምናሻሽል በተቀመጠው ውል መሰረት የተፈጸመ ነው፡፡ተብሎ ምላሽ የተሰጠው ያያዛቹት አባሪ የጥበቃ ስራ ነው፡፡ነግር ግን እኛ የጠየቅነው የፅዳት ስራ፣ የምግብ ዝግጅት እና የመስተንግዶ አገልግሎት ነው ስለዚህ ምንም አይነት የዋጋ ለውጥ የማይኖር መሆኑን በውሉ ላይ በግልፅ ተቀምጠዋል፡፡ በመሆኑም ክፊያው አግባብ የሌለው በመሆኑ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.7.1 <u>ግኝት፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት በሚመለከት፣</u>

የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 9 ላይ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች ማንኛውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ ዕቃ ወደ መ/ቤቱ ዕቃ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ/ሞዴል 19/ መያያዝ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ የውስጥ ኦዲት ማንዋል ክፍል 4 ክምችት ላይ የሚገኝ ዕቃዎች አስተዳደር እና ቁጥጥር ንዑስ ቁጥር 4.2 ተራ ቁጥር 2 በግዥ፣ በእርዳታ፣ በውርስ እና በተመሳሳይ መንገዶች የተገኙ ዕቃዎች ወደ ግምጃ ቤት ገቢ ከመደረጋቸው በፊት የገቢ ደረሰኝ ሊቆረጥ እንደሚገባ ይገልፃል፡፡ በዚህም መሠረት ኦዲት ስናከናውን በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 226165 በሂሳብ መደብ 6255 ብር 1,396,148.00 ብዛቱ 4 ኮንቴነር የህክምና ዕቃዎች ከሁማን ብሪጅ በእርዳታ ለመጣ የትራንስፖርት ወጪውን ለድርጅቱ ሲከፍል ንብረቱ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት ተገኝቷል፡፡

2.7.2 <u>ስጋት፣</u>

ዩኒቨርሲቲው ላወጣው ወጪ ተመጣጣኝ አገልግሎት ሳያገኝ ክፍያ ከመፈጸሙም በላይ የመንግስት ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ ላይውል ይችላል ።

2.7.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ለዩኒቨርሲቲው ንብረቶቹ ለመግባታቸው የሚገልፅ ማስረጃ ሳይኖር ክፍያ መፈፀሙ የመንግስትን የግዥ መመሪያና ደንብ ከመጣሱም በላይ አሰራሩ የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት የሚያጋልጥ ስለሆነ ክፍያ የተፈፀመባቸው ንብረቶች ገቢ ለመሆናቸው የሚገልፅ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

2.7.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የ2 ኮንቴነር የህክምና እቃ ገቢ ተደርጓል፣ ንብረት ገቢ ደረሰኝ ተያይዟል፡፡

2.7.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ንብረት ገቢ ደረሰኝ ተያይዟል፡፡ ተብሎ ምላሽ የተሰጠው የተቆረጠው የ2 ኮንቴነር ለዛውም ከኦዲት አስተያየት በኃላ በመሆኑ እና የተጠየቀው ግን የ4 ኮንቴነር ስለሆነ

አሁንም መስረጃው ወይም የገቢ መረካከብያ ሞደል 19 ሊቆርጦለት ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ ዓይነት ስራ መቆም አለበት፡፡

## 2.8.1 ግኝት፣ ያለሂሳብ መደቡ የተመዘገበ፣

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝ መመሪ□ ቁ□ር 5/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ተራ ቁጥር 3 የሂሳብ አወቃቀር ስርአት በሚለው ስር የመንግስት መስሪያ ቤቶች የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች በየመደባቸው ተለይተው መመዝገብ እንዳለባቸው መመሪያው ያዛል ፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡-

- ለአምደሚካኤል ተመስገን ጠ/ሥ/ተቋራጭ ምእራፍ 1 ሎት ኤ መሰረተ ልማት ግንባታውን አጠናቆ የመጨረሻ ዙር ርክክብ ስላደረገ በማለት በቀን 12/03/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 919982 የ2.5% መያዣ ሂሳብ /Retention/ ብር 1,240,730.13 የከፈለ ሲሆን ወጪውን በሂሳብ መደብ 5061 የመያዣ ሂሳብ /Retention/ በሚል መመዝገብ ሲገባ በሂሳብ መደብ 6324 ለመሰረተ ልማት ግንባታ በሚለው የተመዘገበ መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲዉ ለተግባር ትምህርት ለሚሄዱ ተማሪዎች ለምግብ ያወጣውን ወጪ ብር **206,167.50** በሂሳብ መድብ 6216 ለምግብ መመዝገብ ሲገባው፣ በሂሳብ መደብ 6231 ለውሎ አበል በሚል የተመዘገበ መሆኑና በዚሁ መልኩ የተማሪዎች የወጪ መጋራት ላይም የሚቀንስ መሆኑ ታውቋል፣

በድምሩ ብር **1,446,897.63** ያለ ሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

## 2.8.2 ስጋት፣

ወጪዎች በተገቢው የወጪ ሂሳብ መደብ ተመዝግበው ሪፖርት ካልተደረጉ የዩኒቨርሲቲውን የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ሊከፍሉት የሚገባ የወጪ መጋራት ላይም ላይከፍሉ ይችላሉ ፡፡

2.8.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የወጪዎች ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ትክክለኛ የወጪ ሂሳብ መደባቸውን የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል። ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ጥንቃቄ ሊደረግና ማንኛውም ክፍያ ሲፈፀም የመንግስት የክፍያ መመሪያዎች ተጠብቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል።

2.8.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የተሰጠውን የማሻሻያ አስተያየት ተቀብለነዋል፣

2.9.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>የወጪ ማስረጃ የሌለው፣</u>

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001፣ በፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 እና በፌዴራል መንግሰት የሂሳብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለማንኛውም ወጪ ክፍያ መፈጸም የሚገባው ተመጣጣኝ የክፍያ ደረሰኝ በማስረጃነት ሲቀርብ ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ዩንቨርስቲው ከኢትዮጵያ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማህበር በባንክ ወጪማስመስያ ቁጥር 599511፣ በቀን 11/12/08 የገዛውን የኮምፒዩተርና የመጽሃፍ ግዥ ብር 681,024.00 የወጪ ደረሰኝ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን ተረጋግጧል።

2.9.2 <u>ስጋት፣</u>

ዩኒቨርስቲው ለፈፀመው ክፍያ ማስረጃ ባለመቅረቡ የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አዳጋች ይሆናል፡፡ አቅራቢዎቹ ገቢያቸውን እንዲደብቁና የሚጠበቅባቸውን ግብር በአግባቡ እንዳይከፍሉ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

2.9.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማናቸውንም ክፍያዎች ከመክፈሉ በፊት ማስረጃ/ማወራረጃ /ሊሆኑ የሚችሉ ህጋዊ ደረሰኞችን ክፍያው ከተፈፀመላቸው አካሎች በመቀበል ከክፍያ ሰነዱ ጋር መያያዙን በማረጋገጥ ክፍያ ሊከፈል ስለሚገባ ከሚመለከተው አካል ማስጀውን በማስመጣት ከወጪው ሰነድ ጋር ማያያዝ ይኖርበታል፡፡

2.9.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ምላሽ አልተሰጠም፡፡

2.10.1 <u>ግኝት፣ ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ፣</u>

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር ሚያዚያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያን በተመለከተ ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ‹‹ለሙሉ፤ ለተጠባባቂ እና ረዳት ፕሮፌሰር 120፤ ለሌክቸረር 100፤ ረ/ሌክቸረር እና ምሩቅ 65 እና ለቴክኒክ ረዳት 45 በዚሁ ተመን ስሌት ብቻ ውል በመዋዋል ያስተማሩበት ክፍያ እንደሚከፈላቸው›› መመሪያው ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርስቲው ለጤና ሳይንስ ኮሌጅ ባለሙያዎች እና ለደብረ ታቦር ሆስፒታል ሀኪሞች የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪዎችን የትርፍ ሰዓት ያስተማሩበት ክፍያ በሚል በድምሩ ብር **965,840.59** ውል ሳይኖር ከመንግስት የክፍያ መመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

2.10.2 <u>ስጋት፣</u>

ከመመሪያና ደንብ ውጭ ክፍያዎችን መፈፀም የመንግስት ውስን በጀት አላግባብ ወጪ እንዲሆን መንገድ የሚከፍት አሠራር ከመሆኑም በተጨማሪ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

2.10.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

አላግባብ ከመመሪያ ውጭ ውል ሳይኖር ለጤና ሳይንስ ኮሌጅ ባለሙያዎች እና ለደብረታቦር ሆስፒታል ሀኪሞች የተከፈለው የኦቨር ሎድ ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት መስራት ይገባል፡፡

2.10.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በውል ላይ የተመሰረተ ክፍያ እንዲሆን ተደርጓል ለቀጣዩ፣

2.11.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ከግዥ መመሪያ ውጭ የተፈጸመ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 የግዥ ዘዴዎችና አፈጻጸማቸው  አንቀጽ 15 የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች ንዑስ አንቀጽ 15.1 በአዋጅና በመመሪያ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው እና የግዥ መመሪያ አንቀጽ 4/ሀ ላይ የመንግስት ግዥ መርሆዎች ውስጥ አንዱ በግዥ አፈጻጸም ረገድ በውድድር ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም ማስገኘት ስለሆነ አስፈላጊውን የገበያ ጥናት ተደርጎ ወይም የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ዋጋን ተንተርሶ ሊሆን እንደሚገባ  ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም አንድ ድርጅት ብቸኛ አቅራቢ የሚባለው በገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተዘጋጀው በአቅራቢ ዝርዝር ውስጥ ለመሆኑ እውቅና ያገኘ መሆኑ ማረጋገጥ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፣

- በ07/06/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 601577 የብር **1,143,847.50** ሁለት የውኃ ፓምፕ ግዢ ከራይት ኤሌክትሪክና የህንጻ መሳሪያዎች ንግድ በቀጥታ ያለውድድር የተፈፀመ ግዥ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- በ16/04/2008 በወጣው ግልጽ ጨረታ ውድድር የላይብረሪ ወንበር በቀን 08/03/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 601001 ብር 5,699,986.00 ለማህበረ ትጉሃን የእንጨትና ብረታብረት ኮንስትራክሺን ስራ እንዲያቀርብ ተደርጎ ክፍያው ተፈጽሟል ፡፡ ሆኖም ግን አሸናፊው ድርጅት አንዱን ወንበር በብር 1,900.00 ሂሳብ 3000 ወንበሮችን በብር 5,699,986.00 ሲፈጽም የገበያ ጥናት ተደርጎ ወይም የማእከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ዋጋን መሰረት ባላደረገ መልኩ የተፈጸመ መሆኑ፡፡ በተጨማሪም አሸናፊ ተብሎ የተሰጠው ይኸው ድርጅት የአስመጭነት ፍቃድ የሌለው መሆኑ እየታወቀ ጨረታውን እንዲያሸንፍ የተደረገ መሆኑ፣

ተረጋግጧል፡፡

### 2.11.2 ስጋት፣

- በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥው ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም አያስገኝም። ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም።
- የመንግሥትም ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል።
- የግዥ መመሪያ ተግባራዊ ባለመደረጉ ዩኒቨርሲቲው ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል።

### 2.11.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማንኛው ግዥዎች የፌደራል መንግስት የግዥ መመሪያን መሰረት ያደረገ መሆን ስለሚገባው ከመመሪያው ውጭ አለአግባብ የተፈፀመው ግዥ ለምን እንደሆነ የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር አስፈላጊውን ማጣራት አድርጎ ሪፖርት እንዲቀርብ ። ለወደፊቱም መመሪያን የተከተለ ግዥ እንዲከናወን ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል።

### 2.11.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

1.በማዕከላዊ ስታስቲክ የገበያ ዋጋ ያልተገኘለት እና በዩኒቨርሲቲ የገበያ ጥናት ባለሙያዎች የዋጋ ጥናት ለማድረግ ቢሞክሩም እቃው ሃገር ውስጥ ሊገኝ ባለመቻሉ እና ከአውስኮድ ዋጋ እንዲሰጡን ጠይቀን ከሰጡን ዋጋ አንጻር የተጋነነ በመሆኑ ጨረታው ታጥፏል፡፡ ቀጥሎም ግዥ ኤጀንሲን በውስን ጨረታ ለመግዛት ጠይቀን በመፈቀዱ 7 ድርጅቶችን ብንጋብዝም በቀኑ የመለሰ 1 ብቻ ነው ይህም ቴክኒካሉን ባለሟሟላቱ ከጨረታው ውጭ ሆኗል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በጣም አሳባቢና የተማሪ ጉዳይ ስለነበር የበላይ ኃላፊዎች ተሰብስበው መጀመሪያ በግልፅ ጨረታ የተወዳደሩትና ተጋኗል ተብሎ ከታጠፈው ጨረታ አቅራቢዎች ፈቃደኛ ከሆኑ ዋጋውም ከዚህ በፊት ከተገዛበት የተሻለ ስለሆነና ሌላ አማራጭ ተሞክሮ ማግኘት ስላልተቻለ የተወሰኑ ተጫራቾችም ፈቃደኛ ሆነው ተገዝቷል፡፡ ስለዚህ ግዥም በግልጽ ጨረታ የተፈጸመ ነው፡፡

2.የላይብረሪ ወንበርን በሚመለከት በግልፅ ጨረታ ወጥቶ ምንም እንኳን ከገበያ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር መጠነኛ የዋጋ መጋነን ቢያሳይም በርካታ ናሙናዎች ቀርበው በቴክኒክ ኮሚቴ ታይተው ጥራታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ውድቅ የተደረገ ሲሆን እንዲሁም ከመከላከያ ኢንጂነሪንግ በቀጠታ ለማሰራት ተፈልጎ በሃገር ውስጥ የተመረተ የተሰጠን ዋጋ ብር 1508.8 ሲሆን ከአሸናፊ ድርጅት ጋር ሲነጻጸር ኢምፖርትድ ኳሊቲ ስለሆነና ዋጋው የተጋነነ ባለመሆኑ የተገዛ ግዥ ነው፡፡

### 2.11.4 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በተራቁጥር 1. ግዥው በግልጽ ጨረታ የተፈጸመ ነው፡፡ ተብሎ ምላሽ የተሰጠው ተቀባይነት የለውም ምክንያቱም በቀጥታ ያለውድድር የተፈፀመ ግዥ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል። በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው ለወደፊት እንደዚህ ዓይነት ስራ መቆም አለበት።

### 2.12.1 ግኝት፣ ጨረታ ከአሸነፈ ድርጅት ግዥ ሳይፈጸም የተገኘ፣

በፌደራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀጽ 4/ሀ የመንግስት ግዥ መርሆዎች ውስጥ አንዱ በግዥ አፈጻጸም ረገድ በውድድር ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም ማስገኘት ስለሆነ አስፈላጊውን የገበያ ጥናት ተደርጎ ወይም የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ዋጋን ተንተርሶ ሊሆን እንደሚገባ ይገልጻል። ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በቀን 16/04/08 በወጣው ግልጽ ጨረታ ውድድር የመጽሐፍ መደርደሪያ (ቡክ ሽልፍ) ብዛት 100፣ ኢንፖርትድ ኦፊስ ሼልፍ ብዛት 200 እና ሶፋ ብዛት 30 በ12/04/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 601222 ብር 3,479,200.00 እና በ28/06/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 600083 ብር 805,000.00 ለደጀኔ ለማ እንዲያቀርብ ተደርጎ ክፍያው ተፈጽሟል ፡፡ ነገር ግን ዩኒቨርሲቲው፡-

- አንደኛ አሸናፊ ሳልህ ሀቢብ አንዱን ቡክ ሼልፍ በብር 4,298.00 አቅርቦ እያለ ለሁለተኛ አሸናፊ ለደጀኔ ለማ በብር 7,500.00 ሂሳብ እንዲያቀርብ በመደረጉ፣ በልዩነት 7,500.00-4,298.00=ብር 3,202.00 የሚታይ

ሲሆን የተገዛው 100 ቡክ ሼልፍ በመሆኑ 3,202.00*100=ብር 320,200.00 አላግባብ እንዲወጣ መደረጉን፣

- አንደኛ አሸናፊ አንዱን ሶፋ በብር 7,989.00 አቅርቦ እያለ ለሁለተኛ አሸናፊ ለደጀኔ ለማ በብር 8,427.00 ሂሳብ እንዲያቀርብ በመደረጉ፣ በልዩነት 8,427.00-7,989.00 = 438.00 የሚታይ ሲሆን የተገዛው 30 ሶፋ በመሆኑ 438.00*30= ብር 13,140.00 አላግባብ እንዲወጣ መደረጉን፣
- አንደኛ አሸናፊ ሉብር ትሬዲንግ አንዱን ኢንፖርትድ ኦፊስ ሼልፍ በብር 3,100.00 አቅርቦ እያለ ለሁለተኛ አሸናፊ ለደጀኔ ለማ በብር 4,025.00 ሂሳብ እንዲያቀርብ በመደረጉ፣ በልዩነት 4,025.00-3,100.00= 925.00 የሚታይ ሲሆን የተገዛው ሼልፍ 200 በመሆኑ 925.00*200= ብር 185,000.00 አላግባብ እንዲወጣ መደረጉን እና

በድምሩ ብር **518,340.00** ከአንደኛ አሸናፊ ባለመገዛቱ አላግባብ የመንግስት ገንዘብ እንዲወጣ ተደርጓል።

2.12.2 <u>ስጋት፣</u>

የግዥ መመሪያ ተግባራዊ ባለመደረጉ ዩኒቨርሲቲው ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል።

2.12.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማንኛው ግዥዎች የፌደራል መንግስት የግዥን መመሪያ መሰረት ያደረገ መሆን ስለሚገባው ከመመሪያው ውጭ አለአግባብ የተፈፀመው ግዥ ለምን እንደሆነ የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር አስፈላጊውን ማጣራት አድርጎ ሪፖርት እንዲቀርብ ማድረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱም መመሪያን የተከተለ ግዥ እንዲከናወን ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል።

2.12.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ጨረታው በወቅቱ ቅሬታ ቀርቦበት የተዘጋጀ በመሆኑና ተወዳዳሪ ድርጅቶች የጨረታ ማስከበሪያውንና የጨረታ ዋጋ ፀንቶ የሚቆይ መሆኑን ፈቃደኝነታቸውን

አራዝመው እንዲልኩልን በደብዳቤ ጠይቀን 1ኛ አሸናፊ የሆኑት ለማራዘምና ውል ለመውሰድ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው ያስያዙት የውል ማስከበሪያ ተወርሶ የ2ኛ አሸናፊ ዋጋ ከወቅቱ የገበያ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ተመጣጣኝ በመሆኑ የተገዛ ነው፣

## 2.13.1 ግኝት፣ ከግዥ መመሪያ ውጭ በውስን ጨረታ የተገዛ፣

በፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ/2002 ክፍል 5 አንቀፅ 24 ተራ ቁጥር 24.1 የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥን በግልፅ ጨረታ ዘዴ መጠቀም እንዳለባቸው  መመሪያው ያዛል፡፡ በዚሁ መመሪያ ክፍል 5 አንቀፅ 23 ተራ ቁጥር 23.4 ሀ ላይ የውስን ጨረታ የግዥ አፈጻፀምን በተመለከተ ግዥውን ለመፈፀም የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ ቢያንስ ለሁለት ጊዜያት ወጥቶ ምንም ተጫራች ያልቀረበ እንደሆነ መመሪያው ቢያመለክትም፣ ዩኒቨርስቲው፡-

- ብር 1,400,000.00  ከናሆምና ዘመናይ ህትመትና ማስታወቂያ ስራ ድርጅት የማስታወሻ ደብተር ህትመት ግዥ፣
- ብር 764,062.00 ከኳንተም አስመጪ ድርጅት የላቦራቶሪ ኬሚካሎች ግዥ፣
- ብር 235,136.59 ከሀሚድ ገለቶ የደንብ ልብስ ግዥ እና
- ብር 364,998.50 ከኤልሳቤጥ ማተሚያ ቤት የባንዲራ ህትመት ግዥ፣

በድምሩ በብር **2,764,197.09** ግዥ የፈፀመ ሲሆን፣ በዘርፉ በቂ አቅራቢ እያለ በግልፅ ጨረታ መግዛት ሲገባ በውስን ጨረታ የተፈፀመ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

## 2.13.2 ስጋት፣

በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥው ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም አያስገኝም፡፡ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ የመንግሥትም ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.13.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማናቸውም ግዥዎች በፌደራል መንግስት የግዥ መመሪያና ደንብ መሰረት እንዲከናወኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.13.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በዋናነት ማንኛውም ግዥ የገንዘብ ጣሪያው በውስን ጨረታ መግዛት እንደሚቻል ግ/ን/ብ/አስ/ኤጀንሲን ተጠይቀን ማብሪሪያ ተሰጥቷል፡፡

2.13.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

በዋናነት ማንኛውም ግዥ የገንዘብ ጣሪያው በውስን ጨረታ መግዛት እንደሚቻል ግ/ን/ብ/አስ/ኤጀንሲን ተጠይቀን ማብሪሪያ ተሰጥቷል፡፡ በሚል ምላሽ ይሰጥ እንጂ ግዥው በግዥው መመሪያ መሰረት ያልተፈጸመ መሆኑን ተረጋግጠዋል፡፡ ዩኒቨርስቲው ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ ዓይነት ስራ መቆም አለበት፡፡

2.14.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ከአንድ አቅራቢና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ካልሆነ የተገዛ፣</u>

የፌደራል መንግስት የግዥ መመርያ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ በአንቀፅ 24 ቁጥር 3 መሰረት በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ ሲፈፀም፣ በውድድሩ ተሳታፊ የሚሆኑት አቅራቢዎች ከሦስት ማነሰ እንደሌለባቸው ይገልፃል፡፡ እንዲሁም የኢፌዲሪ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መመሪያ ቁጥር 27/2002 አንቀፅ 5 በ10/09/2004 በቁጥር 3.0/126/5 በተፃፈ ደብዳቤ በተደነገገው የመመሪያ ማሻሻያ መሰረት ከብር 50,000 በላይ ለሚደረግ ማንኛውም የዕቃ ሆነ የአገልግሎት ግዥ መፈፀም የሚቻለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ከሆኑ አቅራቢዎች መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርስቲው ከአንድ አቅራቢ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ካልሆነ ድርጅት በድምሩ በብር **222,874.00** ከቤተልሄም የቢሮ ማሽኖች ጥገና ከመመሪያው ወጭ የአገልግሎት ግዥ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

2.14.2 <u>ስጋት፣</u>

አስፈላጊነታቸው በመንግስት ታምኖበት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን መተላለፍ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል። እንዲሁም ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል።

2.14.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም። በመሆኑም ለወደፊቱ ዩኒቨርሲቲው ማናቸውም የዕቃም ሆነ የአገልግሎት ግዥ ክፍያ ሲፈጽም፣ በመንግስት የግዥ ደንብና መመሪያ መሰረት ሊሆን ይገባል። የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ተገቢውን ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

2.14.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በአካባቢው በቂ የጥገና ተወዳዳሪ ባለመኖሩ የተፈጸመ ግዥ ነው፡፡ ለወደፊቱ የማሻሻያ አስተያየቱን ተቀብለነዋል፡፡

2.15.1 <u>ግኝት፣ ያለውድድር የቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም ክፍል 4 አንቀጽ 15.4 መሰረት ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያት እና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሰነድ መያዝ ይኖርበታል ይላል። ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡-

- በብር 2,725,514.40 ከሶስት ሆቴሎች የተለያዩ የመስተንግዶ አገልግሎት መፈጸሙ፣
- በብር 1,395,982.94 ከባህር ዳር ፖሊ ፔዳ እ/ብ/ብ/ህ/ማ/ጥ/ስ/ ኢንተርፕራይዝ የመጽሃፍትና የተማሪዎች መታወቂያ ካርድ ህትመት አገልግሎት መፈጸሙን፣
- በብር 427,282.50 ከአርስቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት የዲግሪ ህትመት ክፍያ፣

- በብር 1,169,987.00 ከጎንደር ማተሚያ ድርጅት ለወርክ ሾፕ አገልግሎት የሚውል የቆዳ ቦርሳ ከነህትመቱ የተገዛበት፣
- ብር 254,321.12 ከአማራ ዲዛይን እና ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት የጤና ሳይንስ ኮሌጅ አገልግሎት የሚውል የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና የመጠጥ ፍተሻ ክትትል የመጀመሪያ ዙር ክፍያ፣
- በብር 609,080.50 ከቢራራ ቴዎድሮስና ጓደኞቹ የምግብ ዝግጅት የህብረት የሽርክና ማህበር የአገልግሎት ግዥ፣
- በብር 681,024.00 ለኢትዮጵያ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማህበር የኮምፒዩተርና መጽሃፍ ግዥ፣
- በብር **4,080,326.22** ከተለያዩ ማህበራት ጋር የተለያዩ አገልግሎቶች ግዥ፣

በድምሩ የብር **11,343,518.68** ግዥ በቀጥታ አገልግሎቱን ከሚሰጠው ድርጅት ውል በመዋዋል ያለውድድር ወይም ከሚመለከተው አካል በልዩ ሁኔታ ሳያስፈቅድ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

### 2.15.2 ስጋት፣

- በውድድር ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ሊያሣጣ ይችላል፡፡
- በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥ ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡
- የመንግሥትም ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

### 2.15.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ግዥ ሲያከናዉን የግዥ ደንብና መመሪያን ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ካልተቻለም ከሚመለከተው አካል አገልግሎቱን ለመግዛት ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡ ለወደፊቱም መሰል ስህተቶች እንዳይከሰቱ የእርምት እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

2.15.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሆቴል አገልግሎቶችን በውድድር ላይ ተመስርቶ ግዥ ለመፈጸም ደብረታቦር ከተማ ላይ ሆቴሎች ደረጃ ያልወጣላቸው በመሆኑ በበላይ ኃላፊዎች ሆቴሎችን በመምረጥ ለበጀት አመቱ የተፈጸመ ነው፡፡ ሌሎቹ የተለያዩ ማህበራት /Out source/ የዩኒቨርሲቲው የቦርድ አመራር በማሰወሰን በጥቃቅን ተደራጅተው ከተላኩ ማህበራት የተፈጸመ የአገልግሎት ግዥ ነው፡፡

2.16.1 <u>ግኝት፣</u> <u>አለአግባብ ለሽኝት የወጣ ሂሳብ፣</u>

የፌደራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 6 ሀ የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ሥልጣንና ኃላፊነት በመወጣትና የፀደቀውን በጀት መሠረት ወጪዎችን በመፈጸም በኩል መ/ቤታቸውን የመምራትና የመወከል፣ ፕሮግራሞችና መ/ቤታቸውን የሚመለከቱ ሕጎች በማስፈጸም በኩል ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው ይላል:: ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ለፕሬዝዳንት ፅ/ቤት የቦርድ አመራር የነበሩትን እና ም/ፕሬዝዳንቶችን ለመሸኘት የሚውል ባለ 21 ካራት እያንዳንዱ 10 ግራም የሆነና ብዛቱ 10 የውጭ የአንገት ሀብል ወርቅ የተገዛበት በሚል በ29/10/2009 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 378623 ብር 124,775.00 ከመመሪያ ውጭ ግዥ ፈጽሞ ተገኝቶል::

2.16.2 <u>ስጋት፣</u>

አስፈላጊነታቸው በመንግስት ታምኖበት የወጡ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎችን መተላለፍ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል:: እንዲሁም የመንግሥት ውስን ሃብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል::

2.16.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ያለ አግባብ ወጪ የተደረገው ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል:: የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ተገቢውን ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል::

2.16.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ከዚህ በፊት በኦዲት የማሻሻያ አስተያየት ላይ ገንዘብ በጥሬው መስጠት እንደማይቻል የተገለጸ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በፊት በዩኒቨርሲቲው በቦርድ አመራር በም/ፕሬዝዳንት ለአገልግሎት አመራሮች በአይነት የተሰጠ ነው፡፡

2.17.1 ግኝት፣ ለግንባታ የመያዣ ሂሳብ ሳይመዘገብ ተመላሽ የተደረገ፣

ለኮንስትራክሽንና ለግንባታ ስራዎች የተፈቀደው በጀት ለታቀደለት ዓላማ መዋሉንና ለሂሳቡ አስፈላጊው ቋትና መረጃዎች ተጠናክሮ ሂሳቡ እየተዘጋጀ ክፍያ የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ቀደም ሲል ውሉ የተያዘው በትምህርት ሚ/ር በመሆኑና ፕሮጀክቱ ወደ ዩኒቨርሲቲው ሲዛወር ዩኒቨርሲቲው ፕሮጀክቱን ከመረከቡ በፊት የነበሩ አግባብነት ያላቸው ሰነዶችና መረጃዎች ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ርክክብ ባለመደረጉና በዩኒቨርሲቲውም በመያዣነት የተመዘገበ ሂሳብ ሳይኖር ለአምደሚካኤል ተመስገን ጠ/ሥ/ተቋራጭ ምእራፍ 1 ሎት ኤ መሰረተ ልማት ግንባታውን አጠናቆ የመጨረሻ ዙር ርክክብ ስላደረገ በማለት በ12/03/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 919982 የ2.5% መያዣ ሂሳብ ብር 1,240,730.13 የተከፈለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

2.17.2 ስጋት፣

የበጀት አጠቃቀም ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር እና የመንግሥት ገንዘብ አላግባብ ሊወጣ ይችላል፡፡

2.17.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ፕሮጀክቱን ከመረከቡ በፊት የነበሩ አግባብነት ያላቸው ሰነዶችና መረጃዎች ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል እንዲረከብና ያሉትን ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦቹን በማስረጃው መሰረት በአግባቡ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

2.17.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ውሉ የተያዘው በትምህርት ሚ/ር ቢሆንም ፕሮጀክቱ ወደ ዩኒቨርሲቲው ርክክብ ሲደረግ ዩኒቨርሲቲው ፕሮጀክቱን ከመረከቡ በፊት የነበሩ አግባብነት ያላቸው የውል

ሰነድና የክፍያ ሰነዶችን ዩኒቨርሲቲው በወቅቱ በቤቶች ልማት ተረክቦ የግንባታና የክፍያ ሂደቶቹን በውሉ መሰረት የተፈጸመ ነው፡፡

### 2.18.1 <u>ግኝት፣</u> <u>የጉዳት ካሳ ያልተቀነሰ የግንባታ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ሰኔ/2002 ባወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 16 ንዑስ ቀጥር 25 መሠረት ከመንግሥት መ/ቤቱ ጋር ውል የገባው አቅራቢ በውሉ መሠረት አገልግሎቱን በወቅቱ ባለማቅረቡ በውሉ መጠን ላይ በየቀኑ 1/1ሺኛ የጉዳት ካሳ መክፈል እንደሚገባው እና የጉዳት ካሳው ከውሉ ዋጋ 10 በመቶ መብለጥ እንደሌለበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው የግንባታ ሥራዎች በመመሪያው መሠረት ክትትል የሚደረግባቸውና በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ተጠናቀው አገልግሎት ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ በተለያዩ ተቋራጮች የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ከግንባታ ጽ/ቤቱ በተገኘ መረጃና ትንተና እንዲሁም በመስክ በኦዲት ቅኝት ሲደረግ፣

- አምደ ሚካኤል ጠ/ሥራ ተቋራጭ የውኃ ትሪትመንት ፕላንት/WWTP/ ግንባታ ተጨማሪ ስራን ጨምሮ በብር 142,805,769.48 በተገባ ውል በ445 ቀናት እስከ 01/12/2007 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ቢሆንም እስከ 2009 በጀት ዓመት ሰኔ 30/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 49.33% ላይ የሚገኙ ከመሆኑም በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረበት የውለታ ጊዜ ከ699 ቀናት ወይም ከ1 ዓመት ከ11 ወር በላይ የዘገየ እና የፕሮጀክቱ ግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 142,805,769.48 *699*1/1000= ብር 99,821,232.50 ሲሆን፣ ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌበት 142,805,769.48 * 10%= ብር 14,280,576.95 የጉዳት ካሣ /Liquidation Dameg/ ገቢ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

### 2.18.2 <u>ስጋት፣</u>

- የወጣው የመንግስት የግዥ መመሪያ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል፡፡

- ግንባታዎች በወቅቱ አለመጠናቀቅ በተቋሙ የመማር ማስተማር (በተማሪዎች ቅበላ፣ በተግባር ትምህርት አሠጣጥ) በሌሎችም አገልግሎቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

2.18.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በዩኒቨርሲቲው በመከናወን ላይ የሚገኙ ግንባታዎች ተጠናቀው ለተፈለጉበት ዓላማና አገልግሎት ለማዋል እንዲቻል ተቋራጮች በውል መሰረት ግንባታዎቹን አጠናቀው እንዲያስረክቡ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የጉዳት ካሳውም በውሉ መሰረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

2.18.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በተለያዩ ምክንያቶች ግንባታውን በተሰጠው የጊዜ ገደብ ማጠናቀቅ ያልተቻለ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው እና አማካሪ ድርጅቱ ቅድሚያ ግንባታው መጠናቀቅ አለበት በሚል የሥራ ስምምነት ዋስትና ከሰጠው ብርሃን ባንክ ጋር በመሆን ግንባታውን ለማጠናቀቅ የጋራ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን እያሳሰብን የጉዳት ካሳውን በተመለከተ ቅድሚያ ግንባታው ይጠናቀቅ በሚል ስምምነት እስከአሁን ሂደቱ ያልተጀመረ ሲሆ ወደፊት ከውልና ከመመሪያ አንጻር ከአማካሪ ድርጅቱ እና ከግዥ ኤጀንሲ ጋር በመነጋገር የጉዳት ካሳ የማስከፈል ሂደቱን የምንጀምር መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2.19.1 <u>ግኝት፣ መመሪያ ከሚፈቅደው በላይ የተከፈለ የተለዋጭ ሥራ፣</u>

የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 25 ንኡስ አንቀጽ 25.3 ለተለዋጭ ሥራ የሚታዘዘው የግንባታ ስራ / Variation Order / የገንዘብ መጠን ከመጀመሪያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከ30% /ሰላሳ በመቶ/ መብለጥ እንደሌለበት ያዛል፣ በዚህ መሰረት ለግንባታ ስራ የተከፈለው ክፍያ አግባብነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ዩኒቨርሲቲው ለአባይ ደምሴ ህ/ሥራ ተቋራጭ Lab & Class Room ግንባታን በብር 30,168,566.27 ውል ያሰረ ሲሆን ተለዋጭ ሥራ / Variation Order/ 30% ብር 9,050,569.88 መሆን ሲገባው ብር 12,814,146.40 በመሆኑ 12,814,146.40 -

9,050,569.88 = ብር 3,763,576.53 ለተለዋጭ ሥራ መመሪያው ከሚፈቅደው በላይ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2.19.2 <u>ስጋት፣</u>

በመመሪያ ከተቀመጠው ውጭ ተለዋጭ ሥራ /Variation Order/ ክፍያ መፈጸም የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ወጪ እንዲሆን መንገድ ከመክፈቱም በላይ የወጣውን መመሪያ ጥሰትን ይፈጥራል፡፡

2.19.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በወጣው የመንግሥት አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ መሠረት ዩኒቨርሲቲው የግንባታ ሥራዎች እንዲከናወኑ በማድረግ የህዝብ ሀብት ለብክነት እንዳይጋለጥ ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

2.19.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በመጀመሪያ ለተቋራጩ ውል ሲሰጥ በቀረበው ዲዛይን ሲሆን ወደ ስራ ሲገባ ዩኒቨርሲያዎችን አንዳንድ የዲዛይን ማስተካከያ እንዲደረግ በመፈለጉ የተደረገ የዲዛይን ለውጥ ምክንያት የግንባታ ብር መጠኑ ጭማሪ ያሳየ ሲሆን የተጨማሪ ስራ በአማካሪ ድርጅት በኩል ለማጽደቅ ከዋናው ውል በላይ 30% የብር ልዩነት በመሆኑ ለተጨማሪ ስራ /Variation/ 8,958.33 ውለታ መመሪያውን ሳይሰጥ የተሰራ ነው፣

2.20.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ያለአማካሪ መሐንዲስ የተፈጸመ የማማከር አገልግሎት፣</u>

የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 7 አንቀጽ 28.5 ሀ ለግንባታ ዘርፍ ስራ ክፍያ የሚፈጸመው የስራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሃንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት /Payment Certificate/ መነሻነት ብቻ እንደሆነ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በከፍተኛ ገንዘብ የሚገነቡ ውስብስብ የሆኑ ስራዎች የዩኒቨርሲቲው የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ስራ አስኪያጅ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል/በኮንስትራክሽን ሚ/ር/ የተረጋገጠ አማካሪ መሃንዲስ ለመሆን የሚያስችል ሰርተፊኬትና ፍቃድ ሳይኖራቸው የብር **70,679,377.44** ግንባታዎች የክፍያ ሰነዶችና የክፍያ የምስክር ወረቀት /Payment Certificate/ እያጸደቀ ክፍያ እንደሚፈጸም በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2.20.2 ስጋት፣

የወጣው የመንግስት የግዥ መመሪያ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል፡፡ በግንባታው ሥራ ላይ ችግር ቢከሰት ተጠያቂነት እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

2.20.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማንኛውም ግንባታ ሲከናውን የግንባታው የክፍያ የምስክር ወረቀት /Payment Certificate/ መጽደቅ ያለበት ወይም የማማከር ስራው መሰራት ያለበት ፈቃድ ባለው አማካሪ መሃንዲስ መሆን ሲገባው አለመደረጉ ተገቢ ባለመሆኑ ለወደፊቱ ግንባታው የግንባታ ማማከር ፈቃድ በተሰጠው አማካሪ መሃንዲስ ሊጸድቅ ይገባል፡፡

2.20.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

አብዛኛዎቹ ግንባታዎች ከደብረ ታቦር ከተማ ውጭ በተለያዩ ቦታዎች እና ዋጋቸውም ዝቅተኛ ስለሆነ አማካሪ ልናገኝ አንችልም በማለት በራሳችን የሰራነው ሲሆን ይህንን አሠራር ወደ ፊት እናስተካክላለን፣

3. የተሰብሳቢ ሂሳብ፣

3.1 ግኝት፣

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሠራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ በተጨማሪም በመመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5/መ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይሁንና የዩኒቨርሲቲው የተሰብሳቢ ሂሳብ በመመሪያው መሠረት

በወቅቱ መወራረዱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሰኔ 30/2009 በሪፖርቱ ከሚታየው ብር 81,255,665.36 ውስጥ፡-

- በሂሳብ መደብ 4210 በመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች /Other Advance Within Government/ ብር 12,444,001.44 ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 11,273,947.34 ከ1 ዓመት እስከ አራት ዓመት በተሰብሳቢ ተይዞ መቆየቱን፣
- በሂሳብ መደብ 4253 ለዕቃ አቅራቢዎች የተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ/ Advance to supplier/ ብር 18,409,848.34 ዕቃው ገቢ ባለመደረጉ ከ9 ወር በላይ ሂሳቡ ሳይወራረድ መገኘቱን፣
- በሂሳብ መደብ 4354 ከመንግስት መ/ቤቶች ውጭ ለሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች/Other advance outside government/ የተሰጠ ብር 5,445,,643.95 ከአራት ዓመት በላይ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

በድምሩ ብር **35,129,439.63** በደንቡ እና በመመሪያው መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

3.2 <u>ስጋት፣</u>

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረድ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለውን የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፣ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊያደርስ ይችላል፡፡

3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ሊወራረድ የሚችለውን እንዲወራረድ፣ ሊወራረድ የማይችለውን ደግሞ ደንቡ በሚያዘው መሠረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተቋሙ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት በቅድሚያ ወጪ በሚደረጉ ሂሳቦች ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ያሉትን ተሰብሳቢ ሂሳቦች ለማወራረድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በሂደት ላይ ስንሆን እንዲወራረድ የበኩላችንን ጥረት እናደርጋለን፣

4. <u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

4.1 <u>ግኝት፣</u>

የተከፋይ ሂሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ የተከፈሉ ወይም የተወራረዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሂሳብ መደብ በ5028 በመንግስት መ/ቤቶች መካከል ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች /Other payables within government / በሰኔ 30/2009 በሪፖርት ከሚታየው ብር 5,356,012.34 ውስጥ በተከፋይ የተያዘ እና ለትምህርት/ሚ/ር መከፈል የሚገባው ብር 4,450,208.45 ለባለመብቱ ሳይከፈል ከ4 ዓመት በላይ መቆየቱን ተረጋግጧል፡፡

4.2 <u>ስጋት፣</u>

የተከፋይ ሂሳብ ለባለመብቱ ድርጅት፣ መ/ቤት ወይም ግለሰብ በወቅቱ አለመተላለፉ ገንዘቡ ለታቀደለት ዓላማ እንዳይውልና በበጀት አጠቃቀም ላይም ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ ለሚመለከተው አካል መከፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ለወደፊቱም የተከፋይ ሂሳብ ላይ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የማሻሻያ አስተያቱን ተቀብለነዋል፣

5. <u>በጀት፣</u>

5.1 <u>ግኝት፣</u>

የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሦስት ተራ ቁጥር 02(1) ማንኛውም

የመንግሥት መ/ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንደሚገባው ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተመደበው የወጪ በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር በየፕሮግራሞቹ ከ10% በላይ ከመደበኛ በጀት ብር 19,765,255.77 እንዲሁም ከካፒታል ብር 71,555,739.47 በድምሩ ብር **91,320,995.24** ያልተሰራበት በጀት መገኘቱን ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፤

| የሂሳብ መደብ | የተስተካከለ በጀት | | ሥራ ላይ የዋለ በጀት | | ያልተሰራበት በጀት | | ያልተሰራበት በጀት በመቶኛ (%) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6113 | 839,000 | 00 | 713,626 | 00 | 125,374 | 00 | **14.94** |
| 6114 | 1,211,610 | 00 | 1,087,873 | 80 | 123,736 | 20 | **10.21** |
| 6115 | 24,537,000 | 14 | 20,867,209. | 14 | 3,669,790 | 86 | **14.96** |
| 6216 | 56,700,000 | 00 | 48,178,801 | 59 | 8,521,198 | 41 | **15.03** |
| 6256 | 233,400 | 00 | 124,468 | 87 | 108,931 | 13 | **46.67** |
| 6313 | 168,639,620 | 00 | 150,023,618 | 31 | 18,616,001 | 69 | **11.04** |
| 6323 | 100,517,280 | 00 | 47,577,542 | 22 | 52,939,737 | 78 | **52.67** |
| 6416 | 8,700,000 | 00 | 1,483,774 | 83 | 7,216,225 | 17 | **82.95** |

### 5.2 <u>ስጋት፤</u>

ዩኒቨርሲቲው የበጀት አጠቀቀምና አያያዝ ስርዓቱ በአግባቡ ካልተጠቀመ ዓመታዊ ዕቅዱን ሊያዛባ ከመቻሉም በላይ በሌሎች መ/ቤት /ተቋማት/ ሊሰራበት የሚችለውን በጀት በዩኒቨርሲቲው ስም ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ይሆናል።

### 5.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በየወሩ በሥራ ክፍሉ በሚቀርበው የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት መሠረት ተራፊውን በጀት በመ/ቤቱ ስም ተይዞ እንዳይቆይ በሌሎች መ/ቤቶች እንዲሰራበት ሪፖርት እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተቋሙ የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስና በጀት አዋጅ መሠረት መጠቀም ይኖርበታል፡፡

5.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በውጭ ምንዛሬ ችግር ምክንያት ውል የወሰደባቸው እቃዎች በወቅቱ ባለመድረሳቸው በጀቱን መጠቀም ያልቻልን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

## 6. <u>ንብረት፣</u>

### 6.1.1 <u>ግኝት፣</u>

በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 1 መሠረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልግሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለባቸው ያዛል:: በዚህ መሰረት የዩኒቨርሲቲውን የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ በተደረገው ኦዲት፡-

1. <u>ቋሚ ንብረቶችን በተመለከተ፣</u>

- ለእያንዳንዱ ቋሚ ንብረት የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር በመሰጠት በቋሚ ንብረቱ ላይ መለጠፍ ወይም መፃፍ እንደሚገባ በመመሪያው የተገለፀ ቢሆንም፣ ዩኒቨርስቲው ባሉት ቋሚ ንብረቶች ላይ በከፊል መለያ ቁጥር ያልለጠፈ ወይም ያልፃፈ መሆኑን፣

2. <u>በንብረት ክፍል ውስጥ ያሉ እቃዎችን አያያዝና አመዘጋገብን በተመለከተ፣</u>

2.1 <u>የቋሚ ዕቃዎች ንብረት ክፍል በሚመለከት፣</u>

- በቋሚ ዕቃ ንብረት ክፍል ውስጥ ዕቃዎቹ ባሉበት አካባቢ ቢን ካርድ ያለ ቢሆንም ዕቃዎቹ በሚገቡበትና በሚወጡበት ግዜ ከዕቃዎቹ ጋር ተገናዝቦ የማይመዛዘን መሆኑን፣
- በ2008 በጀት ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ እጅግ ብዛት ያላቸው የኮምፒተር ጠረጴዛዎች፣ በ2007 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚውሉ የህክምና መሳሪያዎች /model of course of delivery XC-402 ብዛት 5፣ HP ስካነር በ2009 ዓ.ም ተገዝተው ህዳር 26 ገቢ የተደረጉ ብዛት 12፣ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ያሉ ባይንዲንግ ማሽኖች ብዛት 6 አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የተቀመጡ መሆናቸው፣

- በንብረት ክፍል ውስጥ ያሉ 2 የልብስ ማጠቢያ ማሽኖች /ላውንደሪዎች/፣ ሪዞ /Riso / የፎቶ ኮፒ ማሽኖች እና 1 ፍሪጅ ቢንካርድ ተሰርቶ ዕቃዎቹ ባሉበት አካባቢ ያልተቀመጠ መሆኑ፣
- የላብራቶሪ ወንበሮች ብዛት 210፣ የመፅሀፍት መደርደሪያዎች ብዛት 100 እና ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚውሉ ነጭ ሰሌዳዎች ብዛት 200 በ2009 ዓ.ም በጀት ተገዝተው አገልግሎት ላይ ሳይውሉ ተቀምጠው መገኘታቸው፣

2.2 <u>የአላቂ ዕቃዎች እስቶርን በተመለከተ፣</u>

- በአላቂ ዕቃዎች ንብረት ክፍል ውስጥ ዕቃዎቹ ባሉበት ቦታ ቢን ካርድ/ በሀርድ ኮፒ/ተቀምጦ ዕቃዎች ገቢና ወጪ በሚሆኑበት ወቅት እየተመዘገበ የማይመዛዘን መሆኑ፣
- ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ የተቀመጠ የሪኮ ቀለም ብዛት 89፣ የፕሪንተር ቀለም ሞዴል 49A ብዛት 10፣ ማጣበቂያ /peacock fic/ ብዛት 803 እሽግ ጣሳዎች፣ በ2009 ዓ.ም ታህሳስ ወር ተገዝቶ የገባ በየዳ የመጸዳጃ ቤት ማጠቢያ መርዝ ብዛት 12,310፣ በ2008 ዓ.ም ሰኔ ወር ተገዝቶ የገባ 295 ፓድ የእጅ ካርቦን፣ በ2008 ዓ.ም መጋቢት ወር ተገዝተው የገቡ ሲዲዎች /CW / ብዛት 1,392.00፣ በ2008 ዓ.ም በጀት ለደንብ ልብስ ተብለው የተገዙ የወንዶች ጫማ ብዛት 631 ጥንድ ጫማዎች በጥራት ጉድለት ምክንያት፣ በ2009 ዓ.ም ታህሳስ ወር ተገዝቶ የገባ የመፀዳጃ ቤት መርዝ /ቢም/ ብዛት 29,700.00፣ በ2009 ዓ.ም መስከረም ወር ተገዝቶ ገቢ የሆነ 500 ሜትር ሰንሰለት፣ በ2008 ዓ.ም ጥቅምት ወር ተገዝቶ ገቢ የተደረገ ለደንብ ልብስ የሚሆን 849 ሜትር ብትን ጣቃ ጨርቅ፣ በ2009 ዓ.ም አገልግሎት ላይ እንዲውል ተገዝቶ የተሰፋ ብዛት ያለው የመስኮት መጋረጃዎች በበጀት ዓመቱ ጥቅም ላይ ሳይውል / አገልግሎት ላይ ሳይውሉ/ በንብረት ክፍል ውስጥ የተቀመጡ ከመሆናቸውም በላይ ለክፍሉ ጥበትም ምክንያት መሆናቸው፣
- ለ2009 በጀት ዓመት መጠቀሚያ የሚሆን ሲነር ላይን ደስታ ወረቀት ተገዝቶ ዩኒቨርስቲው ተጠቅሞ ያልጨረሰው መሆኑ እየታወቀ በ2010 በጀት ዓመት

ሌላ ብዛት ያለው ደስታ ወረቀት የተገዛ መሆኑ፣ በ2009 ዓ.ም ጥቅምት ወር ተገዝቶ የገባ 8,873 ፀዲ በረኪና ጥቅም ላይ ውሎ ያላለቀ እያለ በ2010 ዓ.ም ብዛት ያለው በረኪና የተገዛ መሆኑ፣

2.3. **<u>የጥገና ዕቃዎች መለዋወጫ ንብረት ክፍል በተመለከተ፣</u>**

- የንብረት ገቢ ደረሰኝ እና የወጪ ደረሰኝ እንዲሁም ቢን ካርድም ጭምር የሚሰራው በንብረት ግምጃ ቤት ባለሙያው በመሆኑ የንብረት ምዝገባ ቁጥጥር /ስቶክ ካርድ/ የማመዛዘን ስራ ያልተሰራ በመሆኑ ለንብረት መጥፋት/ መጉደል/ ምክንያት የሚሆን አሰራር እየተሰራ መሆኑ፣
- በንብረት ክፍሉ 1,000 ሊትር /በባለ 40 ሊትር 25 ጀሪካዎች / አሲድ የተቀመጠ በመሆኑ አሲዱ በቀላሉ የእሳት አደጋ ሊፈጥር ስለሚችል ለንብረቶች መውደም ምክንያት ሊሆን በሚችል አቀቀማመጥ ከሌሎች የጥገና ዕቃዎች ጋር አብሮ የተቀመጠ መሆኑ፣

2.4. **<u>የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ንብረት ክፍል በተመለከተ፣</u>**

- በንብረት ክፍሉ ዕቃዎቹ ባሉበት ቦታ ቢን ካርድ/ በሀርድ ኮፒ/ ተቀምጦ ዕቃዎች ገቢና ወጪ በሚሆኑበት ወቅት እየተመዘገበ የማይመዛዘን መሆኑ፣
- የንብረት ክፍል ጥበት በመኖሩ ዕቃዎችን ለመለየት በሚያስቸግር አቀማመጥ ተደራርበው የተቀመጡ መሆናቸው፣
- በ2007 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ 38 የተሽከርካሪዎች ሾክ አብዞርበሮች /አሞርዛተሮች/ እና ኤር ክሊነሮች ብዛት 37 እስከ አሁን ድረስ አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የተቀመጡ መሆናቸው,
- በንብረት ክፍል ውስጥ የሚሠራ ኢት 0524 ማያህ /MAYAH/ ሞተር ሳይክል ከ 2 ዓመት በላይ ከተመላሽ /አሮጌ/ ከሆኑ ዕቃዎች ጋር የተቀመጠ መሆኑ፣
- በሶስት ትልልቅ እሽግ ካርቶኖች /በባለ 50 Gross Weight/ ከ11,994 በላይ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያላለፈባቸው የወንድ ኮንደሞች ያለ አገልግሎት ተመላሽ ከሆኑ አሮጌ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ጋር ከ2 ዓመት በላይ ተቀምጠው ያሉ መሆናቸው፣

2.5. <u>የተማሪዎች ክሊኒክን በተመለከተ፣</u>

- በክሊኒኩ ዋና ንብረት ክፍል ውስጥ ቢን ካርድ የሚጠቀሙ ቢሆንም ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ የማመዛዘን ስራ ያልተሰራ መሆኑ፣
- መድሀኒቶች ወደ ዲስፔንሰሪ ክፍል ገብተው ተሰራጭተው ካለቁ በኋላ በድጋሚ ከዋናው ንብረት ክፍል እንዲወጡ ከመደረጋቸው በፊት በትክክል ለታካሚ ተማሪዎች ተሰጥተው ስለማለቃቸው በፕሪስክሪፕሽን ወረቀቶች ትዕዛዝ ወጪ የሆኑት መድሀኒቶች ከዋናው ንብረት ክፍል ወደ ትንሹ ንብረት ክፍል ገቢ ከሆኑት መድሀኒቶች ጋር የሚመዛዘኑበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣

2.6. <u>አገልግሎት የማይሰጡ ተመላሽ የመኪና እና አላቂ ዕቃዎች በተመለከተ፣</u>

- እጅግ ብዛት ያላቸው ልዩ ልዩ የመኪና ተመላሽ አሮጌ ዕቃዎችና አላቂ ዕቃዎች ሳይወገዱ ከ2 ዓመት በላይ ተከማችተው ያሉ መሆናቸው፣

2.7 <u>የተማሪዎች የምግብ ጥሬቃዎችና የማብሰያ ዕቃዎችን በሚመለከት፣</u>

- የተማሪዎች ምግብ ቤት ጥሬ ዕቃ ማከማቻ ውስጥ የአገልግሎት ጊዜው ጥር 30/2009 ያበቃ 12 ኩንታል የምግብ ጨው እና ያገልግሎት ጊዜው ያላለፈ ነገር ግን የመበላሸት ባህሪ በማሳየቱ ጥቅም ላይ እንዳይውል የታገደ 4,000.00 እሽግ የቲማቲም ድልህ ጣሳዎች ያለመፍትሄ የተቀመጡ መሆናቸው፣ እንዲሁም አንድ የሊጥ ማቡኪያ ማሽን ከ1 ዓመት በላይ በብልሽት ምክንያት ያለ አገልግሎት የተቀመጠ መሆኑ፣

**2.8 <u>ዋጋቸው ከብር 1,000.00 በታች የሆኑ ዕቃዎች በተመለከተ፣</u>**

- በህዳር ወር 2009 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ 572 ማከፋፈያዎች እና 1,693 የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫቶች ያለ አገልግሎት በንብረት ክፍሉ ውስጥ ተቀምጠው የተገኙ መሆናቸው፣

ተረጋግጧል፡፡

6.1.2 <u>ስጋት፣</u>

- ተገቢው የንብረት አያያዝ ሥርዓት ተግባራዊ ባለመደረጉ በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት ንብረቶች ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

- እንዲሁም ንብረቶች በአግባቡ ባለመጠበቃቸው ለተጨማሪ ብልሽትና ወጪ ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

### 6.1.3 ማሻሻያ ሀሳብ፣

ከላይ በዝርዝር በተገለፁት የንብረት አያያዝ እና አጠባበቅ በኩል በታዩት ድክመቶች ላይ የሥራ አመራሩ ተገቢውን ክትትል በማድረግ በአግባቡ ባለመቀመጣቸው ለብልሽት በመዳረግ ላይ የሚገኙት ንብረቶች አገልግሎት ላይ እንዲውሉ እና ሊወገዱ የሚገባቸው ንብረቶች ላይም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

### 6.1. 4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

- የማሻሻያ አስተያየቱን ተቀብለነዋል፣
- የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው የምግብ ጥሬ ዕቃ እንዲወገዱ ተደርጓል፣
- ንብረቶች በቅርብ ተገዝተው የገቡ እና ሳይከፋፈሉ በኦዲት ወቀት የታዩ ሲሆን ወዲያውኑ ተሰራጭተዋል፣

### 6.2.1 ግኝት፣

የፌደራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 እያንዳንዱ ተሽከርካሪ ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ፣ ዘይት እና ቅባት ፍጆታ መጠን፣ የጥገና ወጪ፣ የተጓዘው ኪ/ሜ መጠን በእነማን ስር እንደነበር ….ወዘተ እና ሌሎችም አካቶ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት የዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪ መኪናዎች አስተዳደር ኦዲት ሲደረግ፡-

- ዩኒቨርሲቲው ካሉት 33 ተሽከርካሪ መኪናዎች ውስጥ በኪ/ሜትር የሚጠቀሙት ነዳጅ ከልኬቱ ጋር ሲመዛዘን 29 ተሽከርካሪ በመብለጥ እና 4 ተሽከርካሪ በማነስ የሚያሳይ በመሆኑ የልኬቱን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያላስቻለ መሆኑ፣

- የሰሌዳ ቁጥር ኢት-④-18517 ኢቬኮ ቱርቦ የጭነት መኪና  ሊብሬ የሌለው መሆኑን፣
- ሞተር ሳይክል ያማሃ ኢት-④-0524 ያለአገልግሎት ከሁለት ዓመት በላይ የተሽከርካሪ መለዋወጫ ንብረት ክፍል ውስጥ ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፣

  ተረጋግጧል፡፡

6.2.2 <u>ስጋት፣</u>

የተሽከርካሪ መረጃ አያያዝ መኪናዎች በኪ/ሜትር የሚጠቀሙት ነዳጅ በአግባቡ እየተመዘገበ፤ ሂሳቡ እየተሰላ እና እየተቀናነሰ የሚረጋገጥበት አሰራር በተገቢው መልኩ ታሳቢ ካልተደረገ መንግስት ለነዳጅ የሚያወጣው ወጪ ለብክነት ሊዳረግ የሚችል እና ለብልሹ አሰራር እንዲጋለጥ ሊያደርግ  ይችላል፡፡

6.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የተሽከርካሪ የነዳጅ ልኬት ከሚመለከተው መ/ቤት ጋር በመመካከር በባለሙያ የተደገፈ በሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሚሄድ ታውቆ በሱ መሰረት ስሌቱ በትክክል መሰራት ይኖርበታል፡፡ ሊብሬ ያልወጣለትም አስፈላጊውን ክትትል ተደርጎ ሊብሬ እንዲወጣለት እንዲደረግ፣ በተጨማሪም ያለአገልግሎት የተቀመጠው ሞተር ብስክሌት አገልግሎት ላይ እንዲውል መደረግ ይኖርበታል፡፡

6.2. 4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ሊብሬ የሌለው መኪና በተመለከተ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጋር በመጻጻፍ ላይ ነን፣

6.3.1 <u>ግኝት፣</u>

የፌደራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ያከናወኗቸውን የግንባታ ስራዎች እንደቋሚ ንብረቶች በተለየ መዝገብ መመዝገብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው በጀት የተሰሩ ህንጻዎች በዋናው ግቢ፣ በደብረ ታቦር ሆስፒታል፣ በአዲስ ዘመን ሆስፒታል፣ በእስቴ ሆስፒታል፣ በግንቦት 20 ጤና ጣቢያ፣ በደብረ ታቦር ጤና ጣቢያ፣

በህዳር 11 ጤና ጣቢያ እና በአውዘት ምርምርና አገልግሎት ህንጻዎች ግንባታቸው ተጠናቆ ርክክብ ሲደረግ፣ በመመሪያው መሰረት እንደቋሚ ንብረቶች በተለየ መዝገብ ያልተመዘገቡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

6.3.2 ስጋት፣

የመንግስት መመሪያን ተግባራዊ ከአለመሆኑም በላይ ለብላሹ አሰራር ያጋልጣል፡፡

6.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በመመሪያው መሰረት ዩኒቨርሲቲው ህንጻዎቹን ከተረከበ ግዜ ጀምሮ እንደቋሚ ንብረቶች በተለየ መዝገብ መዝግቦና አስፈላጊው የእርጅና ቅናሽ ሊሰራለት ይገባል፡፡

6.3.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የማሻሻያ አስተያየቱን ተቀብለነዋል፣

7. ልዩ ልዩ፣

7.1.1 ግኝት ፣ የውስጥ ኦዲትን በተመለከተ፣

የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 አንቀጽ 8/2 የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል ተገቢው የሙያ ብቃት፣ ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች የማደራጀትና በቂ የትምህርት ዝግጅትና አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያካበተ የውስጥ ኦዲት በመ/ቤት የመመደብ ኃላፊነት እንዳለበት ይገልፃል፡፡ በዚህ መሠረት በመዋቅሩ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የሰው ኃይል በተመለከተ አራት ፋይናንሻል ኦዲተር፣ ሶስት የክዋኔ ኦዲተር እና ሁለት የንብረት ኦዲተር እንደሚያስፈልገው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት ክፍል በመዋቅሩ በተፈቀደው መጠን በሰው ሀይል ያልተደራጀ መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

7.1.2 ስጋት፣

- በፌዴራል መንግስት የተዘረጋውን የቁጥጥር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ከሚያስችለው ደጋፊ የአስተዳደር ዘርፍ ሊያገኝ የሚገባውን አገልግሎት በአግባቡ እንዳያገኝ ምክንያት ይሆናል፡፡

- በውስጥ የቁጥጥርና ክትትል ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

7.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው ክፍሉ የሚጠበቅበትን አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የሰው ኃይሉ እንዲሟላ ተገቢውን ጥረት እንዲያደረግ እና ክፍሉ የሚጠበቅበትን ውጤት እንዲያስገኝ በባለሙያ እንዲጠናከር ሊደግፈው ይገባል፡፡

7.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ሙሉ መዋቅሩ አንደ ጊዜ ማሟላት ያስችላል፣ በሂደት እናሟላለን፡፡

7.2.1 <u>ግኝት፣</u> <u>የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ላይ እርምጃ አወሳሰድ፣</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምሰት አንቀጽ 17/3 መሰረት ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሀሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡ የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው፡፡ በዚሁ መሰረት የ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ መወሰዱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- ብር 2,500,000.00 ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመለት ዓላማ ውጭ ለሆነ የሥራ ዘርፍ ከመደበኛ ባልተፈቀደ በጀት ወጪ በማድረግ አለአግባብ የአክስዮን ግዥ መፈጸመ መሆኑና  ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ፣
- በ27/01/2007 በቁጥር በጠ1/6/39 ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተላለፈ መመሪያ መሰረት በመንግስት ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ ተማሪዎች ካለው ነባራዊ ሁኔታ አኳያ በመገምገም ከመስከረም 1ቀን 2007 ጀምሮ የምግብ በጀት ተመን በተማሪ በቀን ብር 15 እንዲሆን የተወሰነ

ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው ለ2ኛ እና ለ3ኛ ዓመት ህክምና አንስቴዥያን ሚድዋይፈሪ ተማሪዎች በቀን ብር 35 እንዲሰጣቸው በመደረጉ እና ለእያንዳንዱ ተማሪ ብር 20 በተጨማሪ በመከፈሉ በድምሩ ብር 242,800.00 ከተመን በላይ ወጪ መደረጉና አለአግባብ በብልጫ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ፣

- የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ/በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ቢወስንም ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 137,999.96 የማበረታቻ እና ሽልማት ክፍያ ፈፅሞ መገኘቱና አለአግባብ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ፤

የኦዲት አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ ያልተውሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

### 7.2.2 ስጋት፣

በኦዲት በሚሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች መሠረት ዩኒቨርሲቲው የእርምት እርምጃ የማይወስድ ከሆነ በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ዘንድ ግልፅነትና ተጠያቂነት ማስፈን አይቻልም፡፡ የመንግሥት ገንዘብና ንብረትም እንዲመዘበር መንገድ ይከፍታል፡፡ በተጨማሪም መንግሥት የሚያወጣቸው አዋጅ፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይከበሩ ይችላሉ፡፡

### 7.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር በኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳቦች መሠረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ ግልፅነትና ተጠያቂነት ማስፈን ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆነም በ2008 በጀት ዓመት በኦዲት በተሰጡ አስተያየቶች መሠረት የእርምት እርምጃ ተወስዶ ሪፖርት እንዲቀርብ በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

### 7.2.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ምላሽ አልተሰጠበትም፡፡

## በመጨረሻም ለተደረገው የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!!